# የሶማልያ ሰላም የጎረቤቶቿም ሠላም ነው!!

## “ሶማልያን መደገፍ ሰላምን መደገፍ ነው” ዴቪድ ካሜሮን

ዮናስ 05/15/13

ካቻምና የተጀመረው የለንደኑ የሶማልያ ጉባዔ አሁን ፍሬ እያፈራ ይመስላል፡፡ ፀሃፊዎች “የነውጠኞች ገነት” ሲሏት የከረመችው ሶማልያ አሁን “አዲሲቷ ሶማልያ” የሚል ስያሜ አግኝታለች፡፡ ከሠሞኑ የተካሄደውና በሶማልያ ጉዳይ ላይ በመከረው 2ኛው የለንደኑ ጉባዔ ሶማሊያ ተከብራለች፡፡ በለንደኑ ጉባዔ የተወራው እንደከዚህ ቀደሙ የጥይትና ክላሽንኮቭ ጎተራ ስለሆነችው ሶማሊያ አይደለም፡፡ ስለተፈጠሩት መልካም አጋጣሚዎች እና መነቃቃት ስለጀመረችው ሶማልያ እንጂ፡፡ መቀየር ስለጀመረችው ሶማሊያና የመንግሥት ጎጆ ማቋቋም ስለጀመረችው ሶማሊያ እንጂ ተስፋ አጥተውባት ስለነበረው Bronwin Bruton እና Construction engagement ስለተሰኘው ትርክታቸው አልነበረም፡፡

የሶማልያ ጉዳይ ለጎረቤቶቿ ይቅርና ከአፍሪካም አልፎ የአለማችን ጉዳይ ከሆነ በርከት ያሉ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ በተለይም የአልቃይዳ ክንፍ የሆነው አልሸባብ በሶማሊያ ከሚገኘው የፍርድ ቤቶች ህብረት ጋር ጥምረት ፈጥሮ ሦማሊያ በመመሸግ በርካታ ሦማሊያውያንን ለሞትና ለሥደት በመዳረግ፣ የጎረቤት ሃገራትን ሰላምና ጸጥታ በማናጋትና  የአካባቢውን የባህር ላይ ጉዞም ለከፍተኛ የደህንነት ሥጋትና አደጋ ከዳረገበት ጊዜ አንሥቶ ሦማሊያ ለአፍሪካውያንና ለምዕራባውያን መንግሥታት ራስ ምታት ሆና ዘልቃለች፡፡

ታዲያ የአልሸባብና የፍርድ ቤቶቹ ህብረት በሶማሊያ የተቋቋመውን የሽግግር መንግሥት በተፈታተነበት ወቅት አሜሪካ የሽግግር መንግሥቱን በገንዘብና በሎጂስቲክ ሠፋ ያለ ድጋፍ ስታደርግለት ብትቆይም እንኳንሥ የአልቃይዳ ክንፍ ሊንኮታኮት ቀርቶ የሦማሊያውያን በተለይም ወጣቶችና ሤቶች ለሥደት ለሞትና ለሥራ አጥነት የመዳረጋቸው ሂደት ይብሥበት መጣ፡፡

ይኼኔ ነው እንግዲህ ዛሬ  ሶማሊያ የደረሠችበትን ደረጃና የአልሸባብን አከርካሪ መሠበር መገመት የተሣናት ወ/ሮ Bronwin Bruton መጋቢት 2010 ላይ አዲስ የጥናት ወረቀት ከነመፍትሄ ሃሣቦቹ ይዛ ብቅ ያለችው፡፡ ግዙፉ የፖሊሲ ቀያሽና የኢኮኖሚ ተንታኝ በሆነው የአሜሪካ የውጭ ግንኙነት ካውንስል የታተመው የሴትዮይቱ ጽሁፍ “ሱማሊያ አዲስ መንገድ” ይሠኛል፡፡

ይህ የBronwin Bruton ጽሁፍ ባልተረጋጋችው ሦማሊያ በአልሸባብና በፍርድ ቤቶቹ ህብረት ጥምር ጥቃት ፈተና ውስጥ ወድቆ የነበረውን የሶማሊያ የሽግግር መንግሥት ይወቅሳል፡፡ ባጠቃላይ ጽሁፉ

አሜሪካ የአልቃይዳን ክንፍ ለማጥፋትና የሽብርተኝነት መነኻሪያ የሆነችውን ሦማሊያ ከነአልሸባብ ነፃ ለማውጣት የሠጠችውና በመስጠት ላይ ያለችው ረብጣ ምንም አልፈየደም ይላል፡፡

የBronwin ጽሁፍ ይህን ብቻ ብሎ ቢያበቃ ጥሩ መፍትሄም ነው ሲል Construction engagement የተሠኘ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡ ይኸውም የሽግግር መንግስቱ ተስፋ የለሽና አቅመ ደካማ በመሆኑ አሜሪካ ለዚህ መንግስት የምትሠጠውን ገንዘብ ትታና አቁማ አልሸባብን ብታሣምንና ስልጣን ላይ ብታወጣው የተሻለ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

ይህ የBronwin ጽሁፍ በወቅቱ ደጋፊ የነበረው ቢሆንም የሚበዙ ተቃውሞዎችም ገጥመውታል፡፡ ይኸው ዛሬም ጽሁፉን ሲቃወሙ በነበሩት ግለሠቦች ልክ ነበርን የሚያሠኝ ችቦ ተለኩሷል፡፡ ፅሁፉን ሲደግፉ የነበሩትና ፀሃፌዋም ለትችት ተጋልጠዋል፡፡ በለንደኑ 2ኛው የሶማሊያ ጉባዔ፡፡

ከ50 በላይ ሃገራት በታደሙበትና በርካታ ባለድርሻ አካላት የተሣተፉበት የለንደኑ የሶማሊያ ጉባዔ የተመራው በባለ ጉዳዩ የአዲሲቷ ፌዴራላዊት ሶማሊያ ፕሬዝዳንት ሃሰን ሼህ መሃመድና በጋባዧ የብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሮን ነው፡፡ የለንደኑ ጉባዔ የረጅም ጊዜ የትዕግሥት ውጤት መገለጫ የሆኑ ብሥራቶች የተነገሩበትና የወደፊቷን ሶማሊያ በተመለከተ የተመከረበት ጉባዔም ነው፡፡

በዋናነት ኢትዮጵያን ኬንያንና የጎረቤት ጎረቤት የሆነችውን ዩጋንዳ ያካተተው አፍሪካዊው የሰላም አስከባሪ ኃይል ወደ ሶማሊያ እና ወደ አልሸባቡ የበረሃ እሣት ሲያመራ ለጦርነት አምሮት አልነበረም፡፡ ልዩና ከሃገሪቱ ጋር የተያያዘ አጀንዳ ስለነበረው ነው፡፡ አልሸባብና የፍርድ ቤቶቹ ህብረትም ከሦማሊያ በመቀጠል አላማቸው ምን እንደሆነና ፍላጎታቸውም ምን  እንደነበረ በወቅቱ ይፋ ቢያደርጉም በተለይ አንዳንድ መርህ አልባ የሃገሬ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሦማሊያውን ዘመቻ በተመለከተ በምክር ቤቱ ለቀረበላቸው ጥሪ እጃቸውን ሠብስበዋል፡፡ በነገራችን ላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ኢዴፓ የአልሸባብን እና የፍርድ ቤቶቹን ህብረት ዓላማና ቀጣይ ጉዞ ተገንዝቦ በወቅቱ ለመንግስት ጥሪ ያሣየው ድጋፍ የሚዘነጋና መሆን አይኖርበትም።

አልሸባብ የፍርድ ቤቶቹን ህብረት ጠፍሮ የያዘው እንደሚናገረው ለሦማሊያና ሦማሊያውያን ልማትና ነፃነት አልነበረም፡፡ የአልሸባብ ዓላማ ሶማሊያን የአክራሪነት ደዌ የተጠናወታቸው የአንዳንድ አረብ ኃይሎች ቤተ ሙከራ ማድረግ ነው፡፡ በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ የሃይማኖት  ልሂቃኑም ሆኑ ቱጃሮቹ የእንግሊዝን ፕሪሚየር ሊግ ጨምሮ ዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን ቻናሎችን እየለዋወጡ ያያሉ፣ ያሳያሉ፣ ልጆቻቸውንም ያጫውታሉ፡፡ ሶማሊያውያን ሲያዩና ሲጫወቱ ግን እንዴት ተደርጎ በማለት አልሸባብን ጃስ ይላሉ፡፡

የፍርድ ቤቶቹ ህብረት ደግሞ ከአልሸባብ የተሠጠውን ቦንብ ንፁሃን በሆኑት ወንድምና እህቶቹ ላይ ያዘንባል፡፡ ዕድሜ ለአሚሦምና በ "ጥሩ ጎረቤት አታማጣኝ" ብሂል ላደጉት ኢትዮጵያውያን በዛ በበረሃ ባደረጉት ተጋድሎ የአልሸባብ አከርካሪ አሁን ተሠብሯል፡፡ በአናቱም የአልሸባቡ መሪ ፋዙል አብደላ መሃመድ ከተገደለ በኋላ በአልሸባብ መሃል የሥልጣን ሽኩቻ መፈጠሩ አልሸባብን ላይመለሥ ወደመቃብሩ እየነዳው ነው፡፡

አልሸባብና የፍርድ ቤቶቹ ህብረት የሶማሊያ ህዝብ ፍላጎት ቢሆኑ አልሸባብ ባልተመታ ነበር፡፡ የወጣቶች ስደትና የሥራ አጥነት ባልተበራከተም ነበር፡፡ ሴቶችም እንዳይሆኑ ሆነው ባልተጎዱ ነበር፡፡ ስለሆነም ሶማሊያን የአረቦች ቤተሙከራ ለማድረግ ብዙ የለፋውና ብዙ ጉዳት ያስከተለው አልሸባብ ዛሬ ጨርሦ ባይጠፋም አከርካሪው ተሰብሯልና በሶማሊያ በርካታ ለውጦች መጥተዋል፡፡ በሃሰን ሼህ መሃሙድ የሚመራም ፌዴራላዊ መንግሥት ተቋቁሟል፡፡

በኪስማዩና በሌሎችም ቦታዎች ላይ የተመታው አልሸባብ ከመድከሙ ጋር ተያይዞ አረብነት ባህላቸው እንጂ ሃይማኖታቸው ያልሆነው ሶማሊያውያን በባህል እንደሚጋሯቸው አረቦች ፊልም ያያሉ ያሳያሉ፤ ኳስ ይጫወታሉ ማሳየትም ጀምረዋል፡፡ አልሸባብ አሁን የሶማሊያ ያለፈ ታሪክ ሆኗል፡፡ በሦማሊያ ንግድ ቤቶች ከእንቅልፋቸው ፖለቲከኖች ከድብቶቻቸው ወጥተዋል፡፡ እስከነሙስናውና ሥራ አጥነቱም ቢሆን የሶማሊያውያን ተስፋ ለምልሟል፡፡

በለንደኑ 2ኛው የሦማሊያ ጉባዔም በሶማሊያ ስለተፈጠሩት መልካም እድሎችና መ ነቃቃት ተወስቷል፡፡ በዚህ ጉባዔ ላይ አሜሪካ 40 ሚሊዮን ዶላር ለአዲሲቷ ሦማሊ ለግሣለች፡፡ አሜሪካ ይህን ጨምሮ ለሦማሊያና ሦማሊያውያን ሠላምና ዕድገት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብቻ 1.5 ቢሊዮን ዶላር ለግሣለች፡፡

በጉባዔው "በ1990ዎቹ በአፍጋኒስታን ያልሠራነውን በሦማሊያ ልንደግመው አይገባም" ያሉት ዴቪድ ካሜሮን ሃገረ እንግሊዝ 270 ሚሊዮን ዶላር የአውሮፓ ህብረት ደግሞ 58 ሚሊዮን ዶላር በጉባዔው ለሶማሊያ እንኪ ብለዋታል፡፡ በዚህ ገንዘብ እንግሊዝ የሶማሊያውያንን የፖሊስ ሃይል 120 ሺህ ለማድረሥ አቅዳበታለች፡፡ 2013 ከገባ ምንም የባህር ላይ እገታ በሦማሊያ አለመከሠቱ የአልሸባብን መንኮታኮት ያመላከተ ነው ያሉት ዴቪድ ካሜሮን በአልሸባብና በፍርድ ቤቶቹ ህብረት የባህር ላይ ውንብድና የዓለም ኢኮኖሚ 18 ቢሊዮን ዶላር ክሥረት እንደደረሠበት አውስተዋል፡፡

አሁን ሦማሊያውያን አረብነት ባህል እንጂ ሃይማኖት እንዳልሆነ የተገነዘቡት ጎሣዎቿ ቅራኔያቸውን ወዲያ ጥለው መግባባታቸውን ወዲህ ስለማለታቸው ሃሠን ሼህ መሃሙድ ለታዳሚያኑ ይፋ አድርገዋል፡፡ በዚህም ፕሬዝዳንት ሃሠን ሼህ መሃሙድ ይህ የሆነው በአፍሪካውያን የተባበረ

ክንድ አልሸባብ በመመታቱ ነው ሲሉ “አፍሪካ እናመሠግናለን” ብለዋል፡፡ በዚህም የተነሣ አሜሪካ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቷን እና ወዳጅነቷን ከሦማሊያ ጋር በሂላሪ  ክሊንተን አማካኝነት ጠበቅ ማድረግ የጀመረችው ከቅርብ ጊዜ በፊት ነው፡፡ እንግሊዝም 10 ሚሊዮን ህዝብ ባላት ሦማሊያ (ሞቃዲሾ )በውጭ ጉዩ ሚኒስቴሯ ዊሊያም ሄት አማካኝነት ኤምባሲዋን ከፍታ ሌሎቹንም ኑ ሶማሊ.ያ ቢያንስ መቀየር የምትችል ሃገር መሆኗን በመሠረተችው ፌዴራላዊ መንግስት አረጋግጣለች በማለት ጥሪ እያስተላለፈች ትገኛለች፡፡

እንግሊዝ በዚህ ብቻ ሳታበቃ 20 ከመቶ የሚሆነው የአልሸባብ ርዝራዥ  ከሦማሊያ ምድረ ገጽ ይጠፋ ዘንድ በሦማሊያ ጠረፎች ሁሉ ላይ የሬድዮ መገናኛ ልትተክልና ሦማሊያውያን ወታደሮችን በሥልጠና ለመደገፍ ሽር ጉዷን ተያይዛዋለች፡፡ በንግድ የሚታወቀው የሶማሊያ ህዝብ እድሉ ከተሠጠው የት መድረሥ እንደሚችል ዛሬ በሶማሊያ እየተሥተዋለ መሆኑም በጉባዔው ተወስቷል፡፡ “ሶማሊያን መደገፍ ሰላምን መደገፍ ነው” ያሉት ዴቪድ ካሜሮን በሃሰን ሼህ ማህሙድ “ዓለም ሶማሊያ የምትባል አንድ ወዳጅ አግኝታለች ከተባበራችኋት ደግሞ የበለጠ ትሆናለች”  ጥሪ ጥሪውን  በጥሪ አወራርደውታል በጉባዔው፡፡

በጉባዔው የታደሙት የወቅቱ የአፍሪካ ህብረት ሊቀመንበርና የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሣለኝ የአልሸባብን አከርካሪ ለመሥበር የመሪነትን ሚና የተጫወተችው ሃገራቸውን ወክለው ባደረጉት ንግግር፡- ለሦማሊያ እኛም ሆንን ዓለም አቀፉ ማህበረሠብ ድጋፍ እንጂ ሦማሊያውያንን ተክተን መሥራት አንችልም ያሉ ሢሆን ከዚህ ባሻገር ዓለም አቀፉ ማህበረሠብ የሚያደርገው ማናቸውም ድጋፍ በኢጋድ በኩል መሸከርከር እንዳለበትና የመሪነቱንም ሚና ለኢጋድ መስጠት ተገቢ እንደሆነ ያቀረቡት ሃሣብ በመላው የለንደኑ ጉባዔ ታዳሚያን ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ያሉት ሃይለማርያም ደሣለኝ “እሾህን በሾህ” ስለሆነ፡፡

ከ2006 ጀምሮ ሶማሊያን እንምራ ያሉት አልሸባብና የፍርድ ቤቶች ህብረት ኢትዮጵያን ጠልተዋል፡፡ በጥሩ ጎረቤት አታሣጣኝ ባህል የኖረችው ኢትዮጵያ ደግሞ ጥሩ ጎረቤት የሆኑትን ሶማሊያውያንና የሽግግር መንግስት ወዳ አሁን ፍሬዋን በማየት ላይ ትገኛለች፡፡ ጉርብትና አይደለም የጎረቤት ጎረቤትም አታሣጣኝ ያለችዋ ዩጋንዳም ነች ዛሬ ፍሬዋን በመልቀም ላይ የምትገኘው፡፡ በርግጥም ጥሩ ጎረቤት አታሣጣኝ ማለት ደግ ነው ለካንሥ፡፡

ሂዝቦላህ ችግር የሆነባት ሊባኖስ በጎረቤቷ  የሦሪያ አመጽ  ችግሯ ተባብሷል፡፡ እነ ማሊ ዛሬ የታመሡትና ያ ሁሉ ውድመት የደረሠባቸው በጎረቤታቸው ትሪፖሊ አመጽና ከመሃመድ ጋዳፊ ውድቀት ጋር ተያዞ ከሊቢያ  በገፍ በተጓጓዘው  የጦር መሣሪያ አማካኝነት ነው፡፡

የአሜሪካንን እርዳታ ላለማጣት ነው ተባባሪ የሆነችው የተባለላት ፓኪስታን ምናልባትም ከልቧ ባልሆነ ትብብሯ በአፍጋኒስታን የመጣ ለውጥ ባለመኖሩ አይኗ እያለቀሠ ነው፡፡ ስለሆነም ጥሩ ጎረቤት አታሣጣኝ ብሎም ዝም ማለት ሳይሆን መስዋእትነት መክፈል ተገቢ ነው፡፡

የወደፊቷን ሶማሊያ ለመገንባትና ሦማሊያውያንን ለመታደግ አለም አሁን እጇን ዘርግታለች በትውልድ ሶማሊያዊ የሆነውና በዜግነት እንግሊዛዊ የሆነው የኦሎምፒክ ሻምፒዮናው ሞህ ፋራህም ለሶማሊያ እና ሶማሊያውያን ቀጣይ ዕጣ ፈንታ ፋውንዴሽን አቋቁሟል፡፡ አፍሪካውያንም ረብጣ ዶላሮችን በሦማሊያ ከመለገሥ ባሻገር የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ድጋፍ ለማድረግ በለንደኑ ጉባዔ ቃል ገብተዋል፡፡ በአናቱም ዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ለሦማሊያ ዕውቅና ሠጥቷታል፡፡ ሶማሊያ ከ22 ዓመታት ልፋትና እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ እነሆ እንዲህ ሆነች፡፡ የለንደኑ ጉባዔ ግና በቤልጅየም ብራሥልሥ፣ በአፍሪካ አዲስ አበባ፣ በጃፓን ቶኪዮ ስለ ሦማሊያ ሠላምና እድገት የሚቀጥል እንደሆነ በጉባዔው ይፋ ሆኗል፡፡ የሶማሊያ ሰላም የጎረቤቶቿም ሰላም ነው!! “ሶማሊያን መደገፍ  ሰላምን መደገፍ ነው” ይሏል ይህ ነው፡፡